

# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ

## ማኅበረ ቅዱሳን



**ኑ አብረን እንሥራ ለውጥም እናመጣለን!**



በ2002/3 ዓ.ም ተግባራዊ ለማድረግ ፕሮጀክት የተቀረጸላቸው ገዳማት፣አድባራትና የአብነት ት/ቤቶች



# የፕሮጀክት አህጽሮት

## የገንዘብ ድጋፍ ለሚያደርጉ አካላት የቀረበ





በማኅበራዊ አገልግሎትና ልማት ዋና ክፍል
የቅስቀሳና ገቢ አሰባሳቢ ክፍል
ሐምሌ 2001 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ማውጫ


መግቢያ .......................................................................................................................................... ii

1. የደብረ ባሕርይ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ገዳም የሕንፃ ግንባታ ፕሮጀክት ......................................................1

2. ቅድስት ቤተልሔም ድጓ ማስመስከሪያ ጉባኤ ቤት እና ቤተ መጻሕፍት ግንባታ ፕሮጀክት ....................2

3. ባሌ መካነ ሕይወት አቡነ ተ/ሃይማኖት ገዳም የዘመናዊ ከብት ርባታ ማስፋፊያ ፕሮጀክት .....................3

4. የከሳቴ ብርሃን አቡነ ሰላማ ገዳም የመዋዕለ ሕፃናት እና አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮጀክት ......................4

5. የጎንደር መንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም የጉባኤ ቤት የዳቦ ቤት ፕሮጀክት ........................................5

6. ሰገዲ ቅ/ሚካኤል ወዘተጠምቀ መድኅን ገዳም የወፍጮ ፕሮጀክት.............................................................6

7. አሰቦት ደብረ ወገግ አባ ሳሙኤል እና ቅድስት ሥላሴ ገዳም የከብት ማድለብ ፕሮጀክት.......................7

8. የደብረ ጽጌ ማርያም ገዳም የአብነት ት/ቤት ግንባታና ጥገና ፕሮጀክት ..................................................8

9. ደብር ቅዱስ ደብረ መዓዛ አቡነ ተ/ሃይማኖት ገዳም የካህናት ማሰልጠኛ ፕሮጀክት.................................9

10. የብላቴ አውደ ፀሐይ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን የወፍጮ ፕሮጀክት ..............................................10

11. የኪያኬላ አቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም የአብነት ት/ቤት ዘመናዊ የከብት ርባታ ፕሮጀክት...................11

12. የአበልቲ ምዕራፈ ቅዱሳን ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ገዳም የአብነት ተማሪዎች መኖሪያ ቤት ሁለተኛ ዙር ግንባታ ፕሮጀክት.........................................................................................................................12




# መግቢያ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ሥር ተዋቅሮ መንፈሳዊ አገልግሎት በማበርከት ላይ የሚገኘው ማኅበረ ቅዱሳን ከ1992 ዓ.ም ጀምሮ የቤተክርስቲያኒቱ ጥንታዊ ገዳማት ፣ አድባራት እና የአብነት ትምህርት ቤቶች የሚገኙበትን ሁኔታ ለመረዳት በርካታ ጥናቶችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የጥናቱም ዓላማ በእነዚህ ቦታዎች በመገኘት ታሪካቸውን ለመዘገብ፣ ችግሮቻቸውን እና የችግሩን መንስኤዎችን ከመረዳት፣ራሳቸውን ለመቻል የሚያግዙ የልማት ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ ገዳማቱና አድባራቱን ለማጠናከር ነው፡፡

እስካሁን ከተደረጉት ጥናቶችም ለመረዳት እንደተቻለው በሀገሪቱ ብሎም በቤተክርስቲያን ላይ በተደጋጋሚ ጊዜ በተከሰቱ ጦርነቶች፣ የመንግሥት የመሬት ላራሹ አዋጅ፣ የተፈጥሮ አየር መዛባት፣ የምዕመናን አቅም ማነስና ብሎም ለገዳማቱና ለአብነት ት/ቤቶቹ ያላቸው አመለካከት እየቀነሰ መምጣት የገዳማት ዋና ዋናዎቹ የችግሮቻቸው መንስኤ ሆነው ተገኝተዋል ፡፡

በተሰበሰበው መረጃ መሠረት 67 % የሚሆኑት ገዳማትና አድባራት ምንም ዓይነት መተዳደሪያ የሌላቸው እና ለከፋ ችግር የተጋለጡ መሆናቸው፣ 39 % የሚሆኑት ገዳማት እና አድባራት በድርቅ በሚጠቁ አካባቢ የሚገኙ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሎል፡፡ በዚህም የተነሣ ፣ የአብነት መምህራንና ተማሪዎች የአበው መነኮሳት እና ቀሳውስት የኑሮ ደረጃ ከጊዜ ወደጊዜ እያሽቆለቆለ መጥቷል፡፡ ከዚህም በመነሣት ምእመናን በሚፈልጉት መጠን የቤተክርስቲያን አገልግሎት ማግኘት አልቻሉም፣ መነኮሳት በባዕታቸው ጸንተው ባለመኖራቸው የቤተክርስቲያን ቅርሶች ለዘረፋ እና ለስርቆት እየተጋለጡ መጥተዋል፡፡

ማኅበረ ቅዱሳን ከቅዱስ ሲኖዶስ ጸድቆ በተሰጠው ደንብ መሠረት ይህን ችግር በተወሰነ ደረጃ ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ ሰፊ መረሐ ግብር ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡ በመረሐ ግብሩም ፡-

- ገዳማትና አድባራት የአካባቢያቸውን የተፈጥሮ ሀብታት ባማከለ በዘላቂ ልማት በማሳተፍ ራሳቸውን ማስቻል፤ መነኮሳት በባዕታቸው ጸንተው እንዲኖሩ በዚህም መንፈሳዊ እና ታሪካዊ ቅርሶቻቸውን ጠብቀው ለትውልድ እንዲተላለፉ ማድረግ ፣
- የአብነት ት/ቤቶችን የትምህርት ፣የጥናትና ምርምር ማእከልነታቸውን በማጠናከር የካህናት፣ የሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ማፍሪያ፣ የስብከተ ወንጌል እና የሐዋርያዊ ተልእኮ ምንጭ እንዲሆኑ ማድረግ፣
- አስቸኳይ የንዋያተ ቅድሳትና የቀለብ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ገዳማት የገጠር አብያተ ክርስቲያናት ድጋፍ ማድረግ ዋና ዋናዎቹ ናቸው

የበጎ አድራጊ ምእመናን ተሳትፎ እና የገንዘብ ድጋፍ እስካሁን በተሠሩ የልማት ሥራዎች አበረታች ውጤት እየታየ ይገኛል፡፡ የማኅበሩ አባላት እስከ ወረዳ ማእከላት ድረስ ባለው መዋቅር በመኖራቸው ከቅዱሳት መካናቱ በቅርብ ስለሚገኙ በፕሮጀክቶቹ ትግበራ ወቅት ክትትልና ሞያዊ እገዛ ማድረጋቸው ይበልጥ ሥራውን ውጤታማ ያደርገዋል፡፡

ይህን ውጤት አጠናክሮ ለመቀጠል ሁሉም የቤተ ክስቲያኒቱ አካላት በተቀናጀ ሁኔታ መሳተፍ እንዳለባቸ ማኅበረ ቅዱሳን ያምናል፤ ለዚህም ሁሉንም አካላት ማሳተፍ ያስችል ዘንድ ለሚመለከታቸው አካላት መረጃዎችንና የገንዘብ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን የተጠኑ ፕሮጀክቶችን ያቀርባል፡፡

በዚህም ድጋፍ ለሚያደርጉ አካላት በጀታቸው በአማካይ ከ 68,000 እስከ 255,000 ብር የሚፈጁና ከችግሩ ስፋት አንፃር ቅድሚያ ድጋፍ ማግኘት ያለባቸውን 12 ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጅቱን አጠናቆል፡፡ እነዚህን ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ለማድረግና በገዳማቱ ላይ ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት እንዲቻል ምእመናን በጋራም ሆነ በተናጠል የገንዘብና የሙያና የጉልበት ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪውን ያቀርባል፡፡



# 1. የደብረ ባሕርይ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ገዳም የሕንፃ ግንባታ ፕሮጀክት

የደብረ ባሕርይ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ገዳም ከደቡብ ወሎ ሀ/ስብከት በከላላ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ከአዲስ አበባ 600 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ ወደ ገዳሙ ለመሔድ ከከላላ ከተማ በበቅሎ ወይም በእግር እንጂ ሌላ አማራጭ ትራንስፖርት የሌለ በመሆኑ ከከላላ ተነስተው ከ8 ሰዓት የእግር ጉዞ በኋላ ጋስጫ ይገባል፡፡

ይህ ታላቅ ገዳም በአፄ ይስሐቅ ዘመነ መንግስት / 1406-1421/ ኢትዮጵያዊው ቁርሎስ ተብሎው በተጠራው እና በቤተክርስቲያን ከቅዱስ ያሬድ ቀጥሎ ታላቅ ቦታ በያዘው በአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ተመስርቷል፡፡ ገዳሙ በከፍታ ቦታ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ወደ ገዳሙ ለሚዘልቅ ገና ከርቀት በታላቅ ግርማ ሞገስ ይታያል ፡፡ ቤተክርስቲያኑም ከአንድ ወጥ ድንጋይ ተፈልፍሎ የተሰራ ነው ፡፡

ይህ ገዳም ከሃይማኖት ተቋምነቱም ባሻገር የትምህርትና የፍልስፍና ማዕከል ሆኖ አገልግሏል ፡፡ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዛሬ እየተገለገልንባቸው የሚገኙትን በርካታ በመጻሕፍት በዚህ ገዳም ጽፈውልን አልፈዋል ፡፡ መጽሐፈ ምስጢር፣ አርጋኖን፣ሰአታት ወመዓልት ወዘሌሊት ፣ውዳሴ ዘሐዋሪያት በአባ ጊዮርጊስ ከተጻፉት ጥቂቶቹ ናቸው ፡፡

ቀደም ሲል የበርካታ መነኮሳት ባእት የነበረው ይህ ገዳም ለገዳሙ ርስት ጉልት እንዲሆን ከተሰጠው መሬት የሚገኝ ምርት 1/3 /ሲሶ/ መነኮሳቱ ይተዳደሩ ነበር ፡፡ በመሬት ለአራሹ  አዋጅ መሬቱ በመወረሱ ገዳሙ ካለምንም መተዳደሪያ በመቅረቱ እየተዳከመ መጥቶአል፡፡ በቅርብ ጊዜ እንኳን በረኀብ፣ በመጠጥ ውሃ ችግር እና እርዛት የተነሳ 3 መነኮሳት ብቻ በገዳሙ ቀርተው እንደነበር አሁን በገዳሙ ያሉት መነኮሳት ይናገራሉ ፡፡

በአሁኑ ጊዜ በገዳሙ 30 የሚሆኑ መነኮሳት እና 10 የአብነት ትምህርት ተማሪዎች ይገኛሉ ፡፡ መነኮሳቱ ከገዳሙ ከ2 ሰዓት የእግር ጉዞ በኋላ ከሚገኘው የእርሻ መሬት ላይ ከሚገኘው አነስተኛ የሰብል ምርት ውጭ ሌላ ቋሚ መተዳደርያ የላቸውም ፡፡ ይህም ምርት ከዓመት እስከ ዓመት  ለመጠቀም በቂ ባለመሆኑ በየጊዜው የበጎ አድራጊዎችን እጅ ለመጠበቅ ተገደዋል ፡፡ ገዳሙ ከከተማ በጣም የራቀ በአካባቢው ያሉትም ምዕመናን አስራ ስደስት ብቻ  በመቅረታቸው ገዳሙን መደገፍ አልቻሉም ፡፡ የአየር ጠባዩም ቆላማ፣ የሕዝቡም ኑሮ የተበታተነ በመሆኑ በአካባቢው ገቢ ሊያስገኝ የሚችል የልማት ሥራ መሥራት አዳጋች ሆኗአል

ከዚህ በመነሳት ችግሩን በሌላ አማራጭ መፍትሔ ለመፍታት ይቻል ዘንድ ገዳሙ የወረዳው ከተማ በሆነችው በከላላ ከተማ ለኢንቨስትመንት የተመደበ 336 ካ.ሜ ቦታ ተቀብሏል፡፡ ገደሙ ቤተክርስቲያን በወርቃማው ዘመኗ ያገኘችው ታላቅ ታሪካዊ ሥፍራ እንደመሆኑ መጠን መጠበቅ የትውልዱ ግዴታ በመሆኑ በዚህ ቦታ ላይ ለተለያዩ አገልገሎቶች የሚውል ሕንፃ በመሥራት ለገዳሙ ቋሚ ገቢ ማስገኘት የሚያስችል የግንባታ ፕሮጀክት ተቀርጿል፡፡

## የፕሮጀክት አህጽሮት

| | |
|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | የደብረ ባሕርይ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ገዳም የሕንፃ ግንባታ ፕሮጀክት |
| አድራሻ | ደቡብ ወሎ ሀ/ስብከት ከላላ ከተማ |
| የፕሮጀክቱ ዓላማዎች | • ገዳሙ እንዳይፈታና ያለውን የቀደመ ታሪክ ጠብቆ እንዲቆይ ማድረግና ቅርሶችን መጠበቅ ብሎም የቱሪስት መዳረሻ ማድረግ<br>• የገዳሙን የገቢ ምንጭ በማሳደግ መነኮሳቱ በገዳሙ ጸንተው እንዲኖሩ ማስቻል<br>• የአብነት መምህራንንና ተማሪዎችን በስደት ቦታውን ለቀው እንዳይሔዱ ማድረግ |
| የፕሮጀክቱ ባሌቤት | የደብረ ባሕርይ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ገዳም |
| የፕሮጀክቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች | በገዳሙ የሚገኙ መነኮሳት እና ተማሪዎች ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች ሲሆኑ የከላላ ከተማ ነዎሪዎችም ከሕንፃው አገልግሎት ተጠቃሚ ይሆናሉ |
| አስፈጻሚ አካላት | በማኅበረ ቅዱሳን የደሴ ማዕከል እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ |
| ተባባሪ አካላት | የደሴ  ሀ/ስብከት ፣ የከለላ ወረዳ ንግድና ኢንዱስትሪ እና ቱሪዝም ቢሮ |
| የፕሮጀክቱ በጀት | በበጎ አድራጊዎች የሚሸፈን አንደኛ ዙር ________173,812.00<br>በበጎ አድራጊዎች የሚሸፈን አንደኛ ዙር ________228,660.00<br>በማኅበረ ቅዱሳን አባላት ሙያዊ ድጋፍ__________80,494.00 |
| ክትትልና ግምገማ | በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን |



## 2. ቅድስት ቤተልሔም ድጓ ማስመስከሪያ ጉባኤ ቤት እና ቤተ መጻሕፍት ግንባታ ፕሮጀክት

ቅድስት ቤተልሔም በደቡብ ጎንደር ሀ/ስብከት በታች ጋይንት ወረዳ በ16 ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ውስጥ ከአዲስ አበባ 784 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የምትገኝ እጅግ ጥንታዊት ደብር ናት ። አካባቢው ወይና ደጋማ ሲሆን ኮረብታማ ና ተራራ የሚበዛበት ነው። ወደ ቦታው ለመድረስም ከመኪና ወርዶ ፈታኝ የሆነ የ6 ሰዓት የእግር ጉዞ መጓዝ ግድ ይላል።

ቅድስት ቤተልሔም በአገራችን የቤተልሔም ዜማ ጥንታዊና ብቸኛ ማስመስከሪያ ጉባኤ ቤት ናት። በደብሯ ጥንታዊ እና ታሪካዊ የሆኑ ከ100 በላይ የሚሆኑ የብራና መጻሕፍት፣የወርቅ ካባ፣ የወርቅ ለምድ፣የወርቅ አክሊል፣መስቀል እና አልባሳት ይገኛሉ ። ቦታው የድጓ የምስክር ጉባኤ በመሆን ማገልገል የጀመረው በአፄ ሰርጸ ድንግል ዘመን ከግራኝ ወረራ በኋላ ልሣነ እፍረት የተባሉ መምህር በዋሻ አኑረውት በተገኘ የድጓ መጽሐፍ መሆኑ ይነገራል። በትክክል በሚታወቀው ዘመን ይህ ጉባኤ ቤት ለ500 ዓመታት ያህል ኢትዮጵያን ከሌላው ዓለም የሚያስተዋውቃትን የቅዱስ ያሬድ ዜማ ለትውልድ በማሻገር ፣ሊቃውንትን በማፍራት በምስክርነት ቤትነቱ ጸንቶ በማገልገል ላይ ይገኛል ።

ዛሬም ድጓን በመላ አገሪቱ ሲማሩ የቆዩ የድጓ አድራሾች የተማሩትን ትምህርት ለማስመስከር እና ማረጋገጫ ለመቀበል ወደ ቅድስት ቤተልሔም ይጎርፋሉ ። ያሉትን የተለያዩ ችግሮች ተቋቁመው ትምህርታቸውን በሚገባ አጠናቀው ለማስመስከር በቦታው ከ2 እስከ 3 ዓመት ይቆያሉ ። በአሁኑ ሰዓት ተማሪዎቹ ለመማሪያና ለምግብ እህል ማስቀመጫ የሚጠቀሙበት ጉባኤ ቤት በ1976 ዓ.ም የተሠራ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ቤቱ በላያቸው ላይ እየፈረሰ በመገኘቱ በበጋ በፀሐይ፣ በክረምት በዝናብ ምክንያት ጉባኤውን በትክክል ለማካሄድ አዳጋች ሆኖአል። ከዚህም አልፎ ይህ የመማሪያ ቦታ እጅግ ጠባብ ከመሆኑ የተነሣ የሚመጡትን ተማሪዎች በሙሉ ተቀብሎ ማስተማር ስላልቻለ ተማሪዎችን እየመለሰ ይገኛል። ይህን ለእግዚአብሔር ምስጋና የምናቀርብበትንና የምንኮራበትን የቅዱስ ያሬድ ዜማ መጠበቅና ለትውልድም ማስተላለፍ ስለሚገባ ትምህርት ቤቱን ለማጠናከር ጉባኤ ቤቱን ማነጽ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር በመሆኑ የጉባኤ ቤት ግንባታ ፕሮጀክት ተቀርጿል። ይህን ቦታ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ማጠናከር በገዳሙ ላሉት ቅርሶች ጥበቃ ለማድረግ ዓይነተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

### የፕሮጀክት አህጽሮት

| | |
|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | ቅድስት ቤተልሔም ድጓ ማስመስከሪያ ጉባኤ ቤት ግንባታ |
| አድራሻ | በደቡብ ጎንደር ሀ/ስብከት በታች ጋይንት ወረዳ |
| የፕሮጀክቱ ዓላማዎች | • የቤተልሔም ዜማ ምስክርነት የሚሰጥበትን ጉባኤ ቤት በመጠበቅ ከቅዱስ ያሬድ ያገኘነውን ዜማ እንዲስፋፋ ማድረግ፣<br>• ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍል ወደ ቤተልሔም የሚገቡ የድጓ አድራሾች በአግባቡ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ማገዝ፣<br>• አድራሾቹ በትምህርት ቤት ቆይታቸው ከዜማ ትምህርታቸው ባሻገር በሌሎች መስክም እውቀታቸውን አዳብረው እንዲወጡ ማስቻል |
| የፕሮጀክቱ ባለቤት | ቅድስት ቤተልሔም ድጓ ማስመስከሪያ ጉባኤ ቤት |
| የፕሮጀክቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች | 200 አድራሾች እና የደብሯ ካህናት |
| አስፈጻሚ አካላት | በማኅበረ ቅዱሳን የደብረ ታቦር ማዕከል እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ |
| ተባባሪ አካላት | የደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት፣ እና የወረዳው መስተዳድር ጽ/ቤት |
| የፕሮጀክቱ በጀት | በበጎ አድራጊዎች የሚሸፈን__________**20,1027.36**<br>በትምህርት ቤቱ የሚሸፈን ____________**20,000.00**<br>በማኅበረ ቅዱሳን አባላት ሙያዊ ድጋፍ____**60,307.00** |
| ክትትልና ግምገማ | በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን |






## 3. ባሌ መካነ ሕይወት አቡነ ተ/ሃይማኖት ገዳም የዘመናዊ ከብት ርባታ ማስፋፊያ ፕሮጀክት

ባሌ መካነ ሕይወት አቡነ ተ/ሃይማኖት ገዳም በባሌ ጎባ ሀ/ስብከት ከአዲስ አበባ 455 ኪ.ሜ እንዲሁም ከዞኑ ዋና ከተማ ከሮቤ 15 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ከጐባ ከተማ በስተደቡብ በግንፍሌ፣ በስተሰሜን ደግሞ በባሞ ወንዝ መካከል በደን በተሸፈነ ኮረብታማ ቦታ ይገኛል፡፡

ገዳሙ የተመሠረተው በ1987 ዓ.ም. በወቅቱ የሀገረስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በነበሩት በብፁ አቡነ ሰላማ ነው፡፡ ይህ ገዳም በውል አይታወቅም እንጂ ቅድመ ታሪክ እንደነበረው የሚመሰክሩ በውስጣቸው ጽላት እንዳለ /እንደነበረ/ የሚነገርላቸው ጥንታዊ ዋሻዎችና በስርዓተ ቤተክርስቲያን ደንብ የተቀበሩ ብዙ አጽሞች ተገኝተዋል፡፡

በገዳሙ በአሁኑ ሰዓት ከ120 በላይ መነኮሳት እና መነኮሳይያት ይገኛሉ፡፡፡ እንደተመሠረተ መተዳደሪያ መሬት ስለሌለው መናኒያኑ በተደጋጋሚ ለከፋ ረኀብና እርዛት ብሎም ለስደት ተዳርገዋል፡፡ ይህንን ችግር ለመፍታት የሀ/ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በነበሩት አቡነ ሰላማ የአካባቢውን ሕብረተሠብና አንዳንድ በጎ አድራጊዎችን በማስተባበር ለገዳሙ መተዳደሪያ እንዲሆን ዳቦ ቤት፣ የንዋያተ ቅዱሳት መሸጫ ሱቅ፣ የሻይ ቤት፣ ወፍጮ ቤት ለመሥራት የተቻለ ቢሆንም ከመናንያኑ ቁጥር፤ ብዛት እና ከመነሻ ካፒታሉ አንጻር የሚፈለገውን ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል አልሆነም፡፡ በመሆኑም መነኮሳቱ የገበሬዎችን መሬት የእኩል በማረስ፣ የአንገትና የእጅ መስቀሎችን በመስራት ያለውን ችግር ለመቀነስ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡ ገዳሙ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለ በማኅበረ ቅዱሳን የተቀናጀ የልማት ፕሮጀክት የቀረጸ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ የከብት ርባታና አነስተኛ የአትክልት ልማት /መስኖ/ ፕሮጀክት ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ በዚህም ገዳሙ በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ ሆኗል፡፡

የከብት ርባታ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ የሆነው በመጠነኛ ወጪ የመጀመሪያው ምዕራፍ ነበር፡፡ የገዳሙን የገቢ ምንጭ ይበልጥ አስተማማኝ ለማድረግ እና ከዚህም አልፎ ገዳሙን ለሌሎች ገዳማት ሠርቶ ማሳያ ማዕከል ሆኖ እንዲያገለግል የተመረጠ በመሆኑ ለሁለተኛ ምዕራፍ የተሸጋገሩትን ሥራዎች ተግባራዊ ማድረግ አስፈልጓል፡፡ ከዚህም አልፎ ይህ ገዳም ለወደፊት በሀ/ስብከቱ የሚታየውን የቤተክርስቲያን አገልጋይ ጥረት ለመቅረፍ ይቻል ዘንድ የትምህርት ማዕከል ሆኖ እንዲያገለግል ተስፋ የተጣለበት ቦታ ነው ፡፡

### የፕሮጀክት አህጽሮት

| | |
|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | ባሌ መካነ ሕይወት አቡነ ተ/ሃይማኖት ገዳም የዘመናዊ ከብት ርባታ ማስፋፊያ ፕሮጀክት |
| አድራሻ | በባሌ ጐባ ሀገረ ስብከት 01 ቀበሌ |
| የፕሮጀክቱ ዓላማዎች | • ገዳሙ በቂ መተዳደሪያ በማግኘት መነኮሳቱ በባዕታቸው ጸንተው እንዲኖሩ ማስቻል፣<br>• በቤተክርስቲያናችን የገዳማዊ ስርዓት ተጠብቆ ለትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ፣<br>• በገዳሙ የሚሰጠውን የአብነት ትምህርት በማጠናከር በሀ/ስብከቱ ለሚገኙ አብያተክርስቲያናት አገልጋይ ካህናት ማፍራት፣<br>• በገዳሙን ያሉትን የልማት ሥራዎች በማጠናከር አርአያ እንዲሆን ማድረግ |
| የፕሮጀክቱ ባሌቤት | ባሌ መካነ ሕይወት አቡነ ተ/ሃይማኖት ገዳም |
| የፕሮጀክቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች | 120 መነኮሳትና መነኮሳይያት የቅዳሴ ተማሪዎች እንዲሁም የአካባቢው ማኅበረሰብ |
| አስፈጻሚ አካላት | በማኅበረ ቅዱሳን የባሌ ጎባ ማዕከል እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ |
| ተባባሪ አካላት | የባሌ ሀገረ ስብከት፣ የዞኑ ግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ እና ከተማ መስተዳድር |
| የፕሮጀክቱ በጀት | በበጎ አድራጊዎች የሚሸፈን_______132,000.00<br>በገዳሙ የሚሸፈን ________20,000.00<br>በማኅበረ ቅዱሳን አባላት ሙያዊ ድጋፍ____13,200.00 |
| ክትትልና ግምገማ | በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን |






## 4. የከሳቴ ብርሃን አቡነ ሰላማ ገዳም የመዋዕለ ሕፃናት እና አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮጀክት

የከሳቴ ብርሃን አቡነ ሰላማ ገዳም በትግራይ ማዕከላዊ ዞን ሀ/ስብከት ከመቀሌ 40 ኪ.ሜ ከሀገረ ሰላም ከተማ ከአራት ሰዐት የእግር መንገድ በኃላ ይገኛል፡፡ ገዳሙ በአቡነ ሰላማ በአብርሃ ወአጽብሃ ነገስታት በአክሱም ዘመነ መንግሥት የተቋቋመ ሲሆን ረጅም እድሜው ያለው የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ገዳም ነው ፡፡

አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን በኢትዮጵያ የተሾሙ የመጀመሪያው ጳጳስ ሲሆኑ የተሾሙትም በሐዋርያው ቅዱስ አትናቴዎስ ነው፡፡ ስለ ኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ታሪክ ባነሣን ቁጥር አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን በግንባር ቀደምትነት እናገኛቸዋለን፡፡ አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን በአራተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ውስጥ ክርስትናን በኢትዮጵያ ያስፋፉ ብርሃነ ወንጌልን በኢትዮጵያ ያበሩ ሐዋሪያ አባት ናቸው ፡፡ በሀገራችን አብያተክርስቲያናትን በማነጽ፣ ምሥጢር የሚያሳተፉ ካህናትን በመሾም፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሱርስት፣ ከዕብራይስጥ ፣ከግሪክ ወደ ግዕዝ ቋንቋ በመመለስ ታላቅ ሐዋሪያዊ ሥራ ሠርተዋል፡፡ የኝህ ጻድቅና ሐዋሪያ አባት አጽማቸው ያረፈውም በዚሁ በገደሙት ሥፍራ ነው፡፡

በገዳሙ ውስጥ እጅግ ጥንታዊ እና ትልልቅ የብራና መጻሕፍት ይገኛሉ፡፡ ሕንፃ ቤተክርስቲያኑ የአራተኛው ምዕተዓመት የቤተክርስቲያን ጥበብ አሻራና ከድንጋይ ተፈልፍሎ የተሠራ ባለ አራት አምድ ነው፡፡ ሆኖም ግን በጊዜ ብዛት ምክንያት ከማርጀቱ እድሳት ተደረጎለት የማያውቅ ከመሆኑም የተነሣ በአሁን ጊዜ ውሃ በማፍሰስ ላይ ይገኛል፡፡

ገዳሙ በቀዳሚነት ጥንታዊ ብቻ ሳይሆን ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዎሕዶ ቤተክርስቲያን ማንነት አኳያ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ቢሆንም ሊደረግለት የሚገባውን እገዛና ድጋፍ ሊያገኝ ባለመቻሉ ገዳሙ እየተዳከመ መጥቷል፡፡ ገዳሙ በቀዳሚነት ሲጠቀምበት የነበረው ርስት በመሬት ላራሹ አዋጅ ስለተወሰደ በውሰጡ ከነበሩት አበው መነኮሳት አብዛኛዎቹ በምግብ እጦት ምክንያት ተበትነዋል፡፡ በአሁን ጊዜ በገዳሙ ወደ 10 የሚጠጉ መነኮሳት ብቻ ይገኛሉ፡፡

ይህን ችግር ለመቅረፈ ገዳሙን በቋሚነት ሊደግፍ የሚያስችል ሥራ ለመሥራት በዓብያዲ ከተማ 3200 ካሜ ቦታ በመቀበል የመዋዕለ ሕፃናት እና የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመገንባት በገዳሙ እና በማኅበረ ቅዱሳን የመቀሌ ማዕከል በኩል ጥረት ተደርጓል፡፡ ሆኖም ከግንባታ ዕቃ መናር እና በቂ ድጋፍ ማግኘት ባለመቻሉ ሥራው የተወሰነ ደረጃ ከተጓዘ በኃላ የመቋረጥ እድል ገጥሞታል፡፡ በዚህም የተነሣ የከተማው ማዘጋጃ ቤት ሥራው እንዲቀጥል አልያም ቦታውን መልሶ እንደሚወስደው በደብዳቤ አሳውቋል፡፡ ይህ ከመሆኑ በፊት ፕሮጀክቱን በማጠናቀቅ ገዳሙን ተጠቃሚ ማድረግ ስለሚገባ የፕሮጀክቱ ቀሪ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ ዋጋው ተስተካክሎ ቀርቧል፡፡

### የፕሮጀክት አህጽሮት

| | |
|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | የከሳቴ ብርሃን አቡነ ሰላማ ገዳም የመዋዕለ ሕፃናት እና አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮጀክት |
| አድራሻ | በትግራይ ማዕከላዊ ዞን በዓብያዲ ከተማ |
| የፕሮጀክቱ ዓላማዎች | • የማንነታችን አሻራ የሆነውም ጥንታዊ ገዳማችንን መጠበቅ<br>• ገዳሙ በቂ መተዳደሪያ በማግኘት መነኮሳቱ በባዕታቸው ጸንተው እንዲኖሩ ማስቻል፣<br>• በቤተክርስቲያናችን የገዳማዊ ስርዓት ተጠብቆ ለትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግ፣ |
| የፕሮጀክቱ ባሌቤት | የከሳቴ ብርሃን አቡነ ሰላማ ገዳም |
| የፕሮጀክቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች | 10 መነኮሳት የቅዳሴ ተማሪዎች እንዲሁም የአካባቢው ማኅበረሰብ |
| አስፈጻሚ አካላት | ብማኅበረ ቅዱሳን የመቀሌ ማዕከል እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ |
| ተባባሪ አካላት | የትግራይ ማዕከላዊ ዞን ሀገረ ስብከትና፣ የከተማ መስተዳድር |
| የፕሮጀክቱ በጀት | በበጎ አድራጊዎች የሚሸፈን_______170,000.00<br>በማኅበረ ቅዱሳን አባላት ሙያዊ ድጋፍ____25,200.00 |
| ክትትልና ግምገማ | በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን |






## 5. የጎንደር መንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም የጉባኤ ቤት የዳቦ ቤት ፕሮጀክት

የጎንደር መንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም የመጽሐፍ ትርጓሜ ቤት በጎንደር ከተማ ውስጥ ይገኛል:: ይህ ት/ቤት ቅድስት ቤተክርስቲያን ካሏት ጥቂት የመጽሐፍ ትርጓሜ ቤቶች አንዱና ዋነኛው ነው:: ትምህርት ቤቱ በአፄ ፋሲል ዘመነ መንግስት እንደተመሠረተ ይነገራል:: በጎንደር ዘመነ መንግሥት የመጻሕፍት ትርጓሜ ከእጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ጀምሮ ጉባኤው ተስፋፍቶ ሲሰጥ ቆይቷል::

በጉባኤ ቤቱ የሚሰጡት አራቱ ጉባኤያት ማለትም መጻሕፍተ ብሉያት፣ መጻሕፍተ ሐዲሳት፣ መጻሕፈተ ሊቃውንት እና መጻህፍተ መነኮሳት ናቸው:: ቀደም ሲል ጉባኤው ይሰጥበት የነበረውን ቦታ ድርቡሽ አቃጥሎታል:: በአሁኑ ሰዓት ጉባኤው በመምህርነት ሲያገለግሉ በነበሩት እና አራት ዐይና እየተባሉ በሚጠሩት በክቡር ዶክተር አየለ አለሙ መቃብር ቤት ውስጥ ይካሄዳል::

ጥናቱ በተጠናበት ወቅት በቦታው በማስተማር ላይ የሚገኙት ሊቀ ሊቃውንት እዝራ ተጨማሪ ተማሪዎችን ተቀብሎ የማስተማር ከፍተኛ ፍላጎት ቢኖራቸውም ከመተዳደሪያ እጥረት የተነሣ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የሚደጉማቸውን 20 እና በማኅበረ ቅዱሳን መጠነኛ ድጋፍ የሚያደረግላቸውን 10 ደቀ መዛሙርት ብቻ እያስተማሩ ይገኛሉ:: ይህ እየተደረገ ያለው ድጋፍ በቂ ባለመሆኑ ደቀ መዛሙርቱ ትምህርታቸውን በየጊዜው እንዲያቋርጡ ይገደዳሉ:: ከዚህም አልፎ ከመኖሪያ ቤት ችግር የተነሣ አሁን ካሉት ደቀ መዛሙርት ግማሽ ያህሉ ወደ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት እየሔዱ መቃብር ቤት የሚያድሩ በመሆኑ የሌሊቱን ትምህርት ለመቀጸል አልቻሉም::

ለሃይማኖት ምሰሶ የሆኑትን እነዚህ ትርጓሜ ቤቶች ማጠናከር ደቀ መዛሙርትን በበቂ ሁኔታ ማፍራት አስፈላጊ በመሆኑ ይህን ትምህርት ቤት በገቢ ማጠናከር አስፈላጊ ሆኗል:: ለዚህም ትምህርት ቤቱን በገንዘብ ለመደገፍ በሚያስችል የዘመናዊ ዳቤ ቤት ለመክፈት ፕሮጀክት ተጠንቷል:: ለጉባኤ ቤቱ ዳቦ ቤቱ ቢከፈት ለራሱ በቂ የገቢ ምንጭ ከመኖሩም ባሻገር በከተማው የሚታየውን የዳቦ ችግር በመጠኑም ቢሆን ያቃልላል::

**የፕሮጀክት አህጽሮት**

| | |
|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | የጎንደር መንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም የጉባኤ ቤት የዳቦ ቤት |
| አድራሻ | ሰሜን ጐንደር ሀ/ስብከት ጎንደር ከተማ |
| የፕሮጀክቱ ዓላማዎች | • የቤተክርስቲያኒቱ የትርጓሜ ቤቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ማገዝ፣<br>• ደቀ መዛሙርቱ በቂ መተዳደሪያ እንዲኖራቸው ማስቻልና የጉባኤ ቤቱን የመቀበል አቅም ማሳደግ |
| የፕሮጀክቱ ባለቤት | የጎንደር መንበረ መንግስት መድኃኔዓለም የጉባኤ ቤት |
| የፕሮጀክቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች | 45 የሚሆኑ ተማሪዎች እና የከተማው ኅብረተሰብ |
| አስፈጻሚ አካላት | በማኅበረ ቅዱሳን የጎንደር ማዕከል እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ |
| ተባባሪ አካላት | የሰሜን ጎንደር ሀገረ ስብከት፤ የከተማው ንግድና ኢንዱስትሪ ጽ/ቤት |
| የፕሮጀክቱ በጀት | በበጎ አድራጊዎች የሚሸፈን_______118,498.00<br>በማኅበረ ቅዱሳን አባላት ሙያዊ ድጋፍ____17,750.00 |
| ክትትልና ግምገማ | በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን |



## 6. ሰገዲ ቅ/ሚካኤል ወዘተጠምቀ መድኅን ገዳም የወፍጮ ፕሮጀክት

ሰገዲ ቅ/ሚካኤል ወዘተጠምቀ መድኅን የአንድነት ገዳም በአዊ ሀ/ስብከት ከአዲስ አበባ 487 ኪ.ሜ. ከዞኑ ዋና ከተማ ከኢንጅባራ /ኮሶበር/ 50 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ አዊ በአማራ ክልል የሚገኝ ልዩ ዞን ሲሆን የአገው ሕዝቦች መኖሪያ ነው፡፡ ገዳሙ በ1666 ዓ.ም በአቡነ ተጠምቀ መድኅን የተመሠረተ ሲሆን ገዳሙንም የመሠረቱት የአካባቢው ሕዝብ አስተምረው ካጠመቁ በኋላ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ቦታውንም /ቤተክርስቲያኑን/ ለራሳቸው መጸለያ ወይም መስገጃ አስበው መስገጃዬ ናት ብለዋት ስለነበር ከዚያ ጊዜ ጀምሮ አካባቢው ሰገዲ እየተባለ ይጠራል፡፡ ገዳሙም ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አፄ ኃይለሥላሴ ዘመን አካባቢውን የሚያስተዳድረው የገዳሙ መምህር እንደነበር ይነገራል፡፡

በዚህ ገዳም በአሁኑ ሰዓት ወደ 40 የሚጠጉ መነኮሳትና መነኮሳይያት ይገኛሉ፡፡ ገዳሙ በአካባቢው ሕዝብ ዘንድ የማንነት መገለጫ ተደርጎ የሚታይ ቦታ ነው ፡፡ገዳሙ ረጅም ዘመን ያስቆጠረ በመሆኑ በገዳሙ የተለያዩ ቅርሶችም ይገኛሉ፡፡ ይህ ገዳም ማራኪ የሆነ አፀድና መንፈስን የሚያድስ ሰፊ ቦታ አለው፡፡ ገዳሙ የቅዳሴ መምህር ሲኖረው እኝህ አባት ለ30 ዓመታት ቦታው ላይ ያስተማሩ ሲሆን አሁንም ከ15 የማይበልጡ ተማሪዎችን በማሥተማር ላይ ይገኛሉ፡፡ ገዳሙ ለገበሬ ሲሦ በመሥጠት ከሚያሳርሰው መሬት ከሚያገኘው ምርት እንዲሁም በመስኖ ከሚያለሙት ሽንኩራ አገዳ ከሚያገኙት መጠነኛ ገቢ ይተዳደራሉ ፡፡

ገዳሙም ሆነ በአጎራባች ቀበሌዎች የወፍጮ አገልግሎት የሚያገኙት ቢያንስ ሁለት ሰዓት ተጉዘው በቻግኒ ከተማ ሲሆን በከተማ ውስጥ የሚገኙት ወፍጮ ቤቶች በቂ ባለመሆናቸው የገጠሩ ኅብረተሰብም ሆነ ገዳማውያኑ በአህያ ጭነውም ሆነ በእግር ተጉዘው የሚያስፈጩ ሲሆን ወፍጮ ቤት ወረፋ ጠብቀው፣ ባሰቡት ሰዓት ሥራቸውን አከናውነው መመለስ የማይችሉባቸው ቀናት ብዙ በመሆናቸው በመነኮሳቱ የሥራና የአገልግሎት ህይወት ላይ ከፍተኛ ጫና ፈጥሯል፡፡

በተለይ በገዳሙ ከሚገኙት መነኮሳት አረጋውያን የሚበዙ ከመሆናቸው አንፃር ለሌላ ሥራ የሚውለውን የሰው ኃይል ለመቆጠብ እንዲያስችል ይህ የወፍጮ ፕሮጀክት ሊቀረጽ ችሏል፡፡

**የፕሮጀክት አህጽሮት**

| | |
|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | ሰገዲ ቅ/ሚካኤል ወዘተጠምቀ መድኅን ወፍጮ |
| አድራሻ | በአዊ ሀ/ስብከት በቻግኒ ቀበሌ |
| የፕሮጀክቱ ዓላማዎች | • ገዳሙ በቂ መተዳደሪያ በማግኘት መነኮሳቱ በባዕታቸው ጸንተው እንዲኖሩ ማስቻል፣<br>• የአካባቢው ሕዝብ የወፍጮ ችግር በመቅረፍ ለገዳሙ ያለውን የቀና አመለካከት ማጠናከር |
| የፕሮጀክቱ ባለቤት | ሰገዲ ቅ/ሚካኤል ወዘተጠምቀ መድኅን የአንድነት ገዳም |
| የፕሮጀክቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች | በዋናነት ገዳማውያኑን የሚጠቅም ሲሆን ከዚህ አልፎ የአካባቢው ቀበሌዎችም ተጠቃሚ ይሆናሉ |
| አስፈጻሚ አካላት | በማኅበረ ቅዱሳን የቻግኒ ወረዳ ማዕከል፣ እንጅባራ ማዕከል እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ |
| ተባባሪ አካላት | አዊ ሀ/ስብከት |
| የፕሮጀክቱ በጀት | በበጎ አድራጊዎች የሚሸፈን_______114,285.00<br>በማኅበረ ቅዱሳን አባላት ሙያዊ ድጋፍ____16,785.00 |
| ክትትልና ግምገማ | በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን |



## 7. አሰቦት ደብረ ወገግ አባ ሳሙኤል እና ቅድስት ሥላሴ ገዳም የከብት ማድለብ ፕሮጀክት

አሰቦት ደብረ ወገግ አባ ሳሙኤል እና ቅድስት ሥላሴ ገዳም በምዕራብ ሀረርጌ ሀ/ስብከት በሚኤሶ ወረዳ ከአዲስ አበባ በስተምሥራቅ 300ኪ.ሜ ከአሰቦት ከተማ በስተምዕራብ በኩል 18 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ጥቅጥቅ ባለ በተፈጥሮ ደን በተከበቡ ተራራዎች ውስጥ ይገኛል::ገዳሙ የተመሠረተው በፃድቁ በአባ ሳሙኤል ዘደብረ ወገግ ሲሆን እኒህ አባት ከ12ቱ የአቡነ ተ/ሃይማኖት ደቀመዛሙርት አንዱ ናቸው' ይህ ቦታ ጥንት ከክርስቶስ ልደት በፊት የኦሪት መስዋዕት ይሰዋበት የነበረ ቦታ እንደነበረ ይነገራል:: ገዳሙ ጥንታዊ ቢሆንም አባ ሳሙኤል ያሳነጹትን ቤተክርስቲያን በግራኝ ወረራ በመጥፋቱ አሁን ያለውን ቤተክርስቲያን ያሣነፁት በ1952 ዓ.ም አፄ ሃይለ ሥላሴ ናቸው::

ገዳሙ የእናቶችና አባቶች በዓት ያለው ሲሆን አርድእቱንና ደጅ የሚጠኑትን ጨምሮ እስከ 200 የሚደርሱ ገዳማውያን ይኖሩበታል' ቀደም ሲል በተለያዩ ጉባኤ ቤቶች የአብነት ትምህርት በተጠናከረ ሁኔት የሚሰጥ ቢሆንም በአካባቢው በነበረው የአጽራረ ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ ምክንያት በመዳከሙ በአሁኑ ሰዓት አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የቅዳሴና የቅኔ ተማሪዎች ይገኛሉ::

ከዚህም በተጨማሪ በአካባቢው የሚገኙ አብዛኛው አብያተ ክርስቲያናት ከአገልጋይ ካህናት እጥረት የተነሳ በቂ አገልግሎት የሚሰጥባቸው አይደሉም :: ገዳሙ መናንያኑን በአንድነት ማስተዳደር ባለመቻሉ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደ ቁሪትነት ተቀይሮል :: በዚህም በገዳሙ የግል ንበረት እየተስፋፋ በመምጣቱ የገዳሙ አንድነት እየተናጋ መጥቶል:: ከዚህም የተነሳ ገዳሙ ለዘርፈ ብዙ ችግሮች ተጋልጦ ይገኛል:: ለዚህም እንደምክንያት ሆኖ የሚቀርበው ገዳሙ ለመናንያኑ አስፈላጊውን ድርጎ ማቅረብ ባለመቻሉ ነው:: ይህን ችግሮች ከመሰረቱ ለመፍታት ሰፊና የተቀናጀ ፕሮጀክት መቅረጽና መተግበር አስፈላጊ እንደሆነ በማኅበሩ ታምኖበታል:: በአጭር ጊዜ ውስጥ ይህን ችግር ለመቅረፍ እንዲቻል ከተጠኑት ፕሮጀክቶቸ መካከል ዘመናዊ ከብት የማደለብ ፕሮጀክት አንዱ ነው::

የፕሮጀክቱ የመጀመሪያ ምዕራፍ ሥራ ከተለያዩ ድጋፍ አድራጊዎች በተገኘ 97 ሺህ ብር ከ 2001 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እየሆነ ይገኛል:: ይህን ፕሮጀክት አጠናክሮ በመቀጠል ገዳሙን ተጠቃሚ ማድረግ ያስፈልጋል::

### የፕሮጀክት አህጽሮት

| | |
|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | አሰቦት ደብረ ወገግ አባ ሳሙኤል እና ቅድስት ስላሴ ገዳም ከብት ማድለብ |
| አድራሻ | በምዕራብ ሀረርጌ ሀ/ስብከት በሚኤሶ ወረዳ |
| የፕሮጀክቱ ዓላማዎች | • ገዳሙ በቂ መተዳደሪያ በማግኘት መነኮሳቱ በባዕታቸው ጸንተው እንዲኖሩ ማስቻል፣<br>• በቤተክርስቲያናችን የገዳማዊ ስርዓት ተጠብቆ ለትውልድ እንዲተላለፍ ፣<br>• ገዳሙ በተጠናከረ ሁኔታ የትምህርት ማዕከል ሆኖ እንዲያገለግል ማስቻል |
| የፕሮጀክቱ ባለቤት | አሰቦት ደብረ ወገግ አባ ሳሙኤል እና ቅድስት ሥላሴ ገዳም |
| የፕሮጀክቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች | በገዳሙ የሚገኙ 200 የሚሆኑ መነኮሳት |
| አስፈጻሚ አካላት | በማኅበረ ቅዱሳን የአሰበተፈሪ ማዕከል እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ |
| ተባባሪ አካላት | የምዕራብ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት |
| የፕሮጀክቱ በጀት | በበጎ አድራጊዎች የሚሸፈን_______175,000.00<br>በማኅበረ ቅዱሳን አባላት ሙያዊ ድጋፍ____12,540.00 |
| ክትትልና ግምገማ | በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን |



# 8. የደብረ ጽጌ ማርያም ገዳም የአብነት ት/ቤት ግንባታና ጥገና ፕሮጀክት

ደብረ ጽጌ ማርያም ገዳም በሰሜን ሸዋ በሰላሌ ፍቼ ሀ/ስብከት ከአዲስ አበባ በ90ኪ.ሜ ርቀት ላይ በደብረ ሊባኖስ ወረዳ በዋከኔ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ውስጥ ትገኛለች፡፡ ይህች ጥንታዊት ገዳም ፃድቁ አቡነ ተ/ሃይማኖት በ1200ዓ.ም እንደመሠረቷት ይነገራል፡፡ ገዳሟ አገልግሎት እየሰጠች ለብዙ ዘመናት የቆየች ሲሆን ከግራኝ ዘመን በኃላ እስከ 1937ዓ.ም ድረስ ጠፍ ሆና በመቆየቱ ታሪኩ አይታወቅም ፡፡ በቦታ ላይ ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት ታቦት ያልገባበት መቃኞ ቤት አሠርቶ የነበረ ሲሆን አሁን ያለውን ቤተክርስቲያንም ያሠሩት የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ በ1950 ዓ.ም ነው፡፡

ቅዱስነታቸው ከዚህም ባሻገር ቀደም ብሎ በ1939ዓ.ም ታቦቱን ጣሊያን ባሠራው መቃኞ ቤት ውስጥ በማስገባት በቦታው ላይ ሊቃውንትን በማምጣት የንባብ፣ የዜማ፣ የቅኔ፣ የቅዳሴ፣ የዝማሬ መዋስእት እና የመጻሕፍት ትርጓሜ ትምህርት እንዲሰጥ መሠረት ጥለዋል፡፡ ቅዱስነታቸው በተለይም የቤተክርስቲያኒቱ ትምህርት እጅግም ባልተስፋፋባቸው የደቡብና የምዕራብ የሀገራችን ክፍል የሚያገለግሉ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያንን ለማፍራት እንዲቻል በወቅቱ ትምህርት ቤቱን እጅግ ዘመናዊ በሆነ መልክ በማደራጀት ለጉባኤው የመማሪያ ክፍሎች እንዲሁም ለመምህራኑ እና ለተማሪዎች መኖሪያ ቤት ሠርተው በጀትም በመመደብ ይደግፉት ነበር፡፡ ከዚህም በላይ ቅዱስነታቸው ለገዳሚና ለትምህርት ቤቱ መርጃ የሚሆን 300 ጋሻ መሬት ከንጉሡ ነገሥቱ በማስፈቀዳቸው መሬት ላራሹ እስከታወጀበት ጊዜ ድረስ ሲጠቀሙበት ነበር፡፡ ጉባኤ ቤቱም ተጠናክሮ በመቀጠሉ ታላላቅ ሊቃውንትና ጳጳሳትን አፍርቷል ለአብነትም ቀዳማዊ አቡነ ጎርጎርዮስ ፣ አቡነ ኤልሳእ/ያረፉት/፣ አቡነ ቄርሎስ ፣አቡነ ፊልጶስ/ያረፉት/ እና አቡነ ዮሴፍ ይጠቀሳሉ፡፡ አሁንም ይህ ቦታ በተለያዩ ጉባኤያት እስከ 850 የሚደርሱ ከተለያዩ አቅጣጫ የመጡ ተማሪዎች ዕውቀትን የሚያገኙበት ቦታ ነው፡፡

ይህ በእንዲህ እያለ በዘመናዊ መልክ የተደራጀው ጉባኤ ቤት በእርጅና ምክንያት እድሳት ሳይደረግለት በመቆየቱ እንዲሁም ያለአቅሙ በርካታ ተማሪዎችን እንዲያስተናግድ በመገደዱ እየተጎዳና እየፈረሰ ይገኛል፡፡ ከዚህም አልፎ የተማሪዎቹ በአንድ ቤት ታፍገው በመኖራቸው ለተለያዩ በሽታዎች የሚጋለጡበት ሆኗል፡፡ ተማሪዎቹ የመጻዳጃ ቤት የሌላቸው ከመሆኑም በላይ ምግባቸውን የሚያበስሉበት ማእድ ቤት በላያቸው ላይ ፈርሶ ለመውደቅ ቀናትን እየጠበቀ ይገኛል፡፡

ይህ ታላቅ ትምህርት ቤት ከመፍረሱና ተማሪዎቹም ከመበተናቸው በፊት አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ስለሚገባ በአራት ዙር ተከፍሎ የሚሠራ የጥገናና የግንባታ ፕሮጀክት ተቀርጿል፡፡ በመጀመሪያው ምዕራፍ በአሁኑ ጊዜ ለተማሪዎች በማደሪያነት እያገለገለ የሚገኘውን ቤት ማደስ እና ይህ ቤት ከተጠገነ በኋላ በድጋሚ ወደ ብልሽት እንዳይሄድ ተማሪዎች እቃቸውን የሚያስቀምጡበት ቤት እና ለከፋተኛ ችግር የዳረጋቸውን የማብሰያ ቤት መሥራት ነው፡፡

## የፕሮጀክት አህጽሮት

| | |
|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | የደብረ ጽጌ ማርያም ገዳም የአብነት ት/ቤት ግንባታና ጥገና ፕሮጀክት |
| አድራሻ | በሰላሌ ፍቼ ሀ/ስብከት በደብረ ሊባኖስ ወረዳ በዋከኔ ቀበሌ ገበሬ ማህበር |
| የፕሮጀክቱ ዓላማዎች | • ገዳሙ የትምህርት ማዕከል ሆኖ እንዲቀጥል ማስቻል፣<br>• የመምህራኑንና የተማሪዎች የመኖሪያ ቤት፣ የማእድ ቤት ና የመጸዳጃ ቤት ችግር ማቃለል |
| የፕሮጀክቱ ባለቤት | ደብረ ጽጌ ማርያም ገዳም |
| የፕሮጀክቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች | በትምህርት ቤቱ የሚገኙት ወደ 850 የሚጠጉ ተማሪዎችና መምህራን |
| አስፈጻሚ አካላት | በማኅበረ ቅዱሳን የቅዱሳት መካናት ክፍል እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ |
| ተባባሪ አካላት | በሰላሌ ፍቼ ሀ/ስብከት ሀገረ ስብከት፣ |
| የፕሮጀክቱ በጀት | በበጎ አድራጊዎች የሚሸፈን አንደኛ ዙር ________182,562.50<br>በበጎ አድራጊዎች የሚሸፈን ሁለተኛ ዙር ________103,020.00<br>በማኅበረ ቅዱሳን አባላት ሙያዊ ድጋፍ____71,395.00 |
| ክትትልና ግምገማ | በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን |






## 9. ደብር ቅዱስ ደብረ መዓዛ አቡነ ተ/ሃይማኖት ገዳም የካህናት ማሰልጠኛ ፕሮጀክት

ደብር ቅዱስ ደብረ መዓዛ አቡነ ተ/ሃይማኖት ገዳም በአርሲ ሀ/ስብከት በአሰላ ከተማ ይገኛል፡፡ ከ 1986 ዓ.ም. ጀምሮ የደብር ቅዱስ ደብረ መዓዛ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገዳምና የሕፃናት ማሳደጊያ ተብሎ የተሰየመው ይህ ሥፍራ ቀደም ሲል በልዑል አሥራተ ካሣ የተገነባና እስከ ደርግ መንግሥት ድርስ የእንደራሴዎች መኖሪያ ሆኖ ሲያገለግል የቆየ ቦታ መሆኑን የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ ፡፡

በ1978 ዓ.ም. የአርሲ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የሆኑት ብፁዕ አቡነ ናትናኤል በአካባቢው የሚገኙ ወላጅ አልባ ሕፃናትን በመሰብሰብ የሕፃናት ማሳደጊያ ለማቋቋምና የማኅበራዊ ልማት ሥራ ለመሥራት በማሰብ ሥፍራውን በቤተ ክርስቲያን ስም እንዲሠጣቸው ጥያቄ አቅርበው በ1980 ዓ.ም. የክፍለ ሀገሩ አስተዳዳሪ ቦታው ለቤተ ክርስቲያኒቱ እንዲሰጥ በመፍቀዳቸው ካርታ ተሠርቶለት ቤተ ክርስቲያኒቱ በሕጋዊ መንገድ እንድትረከበው ተደርጓል፡፡ ቦታው በምዕራብ አቅጣጫ ከጭላሎ ተራራ በስተግርጌ ሲሆን የቦታው ስፋት በግምት 224.7 ሄክታር የሚሆን ሲሆን ሙሉ በሙሉ በሀገር በቀል የዝግባና ሌሎች የዛፍ ዝርያዎች የተሞላ ነው ፡፡

የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል የወደመውን የግቢውን ገጽታና የፈረሰውን ቤት የተለያዩ በጎ አድራጊዎችን በማስተባባርና በማደስ ለአገልግሎት እንዲበቃ አድርገውታል፡፡ የቤቱ ዕድሣት ከተጠናቀቀ በኋላ በ1986 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ አንድ መቶ ሃያ (120) ዕጓለ ማውታ ሕፃናትን ተቀብሎ የማሳደግ ሥራውን ጀምሯል፡፡ በአሁኑ ሰዓት በቦታው የጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ተሰርቶ በግንቦት 2001 ተጠናቆል ፡፡

በሀገረ ስብከቱ በአገልጋይ ካህናትና ሰባኪ ወንጌል እጥረት ምክንያት መንፈሳዊ አገልግሎት ሳይሰጡ ተዘግተው የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ቁጥራቸው በርካታ ነው፡፡ ይልቁንም ምዕመናንን ከመናፍቃን ትምህርት ለመታደግ እና ከቤተክርስቲያን የተሻለ አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ሰባኪ ወንጌልን ማፍራትና ካህናቱንም ከሚሰጡት የቤተክርስቲያን አገልግሎት በተጨማሪ በማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት እንዲሳተፉ መድረግ አስፈላጊ ነው ፡፡ ለዚህም የካህናት ማሥልጠኛ እና የቴክኒክ ትምህርት ማዕከል በገዳሙ ለማቋቋም የጥናት ሠነድ ተዘጋጅቷል ፡፡ የሥልጠና ማዕከሉም በምዕራፍ ተከፋፍሎ እንዲሰራ ስለታሰበ በመጀመሪያው ዓመት 24 ሰልጣኞችን ተቀብሎ ለማሠልጠን የሚያስችለው ተቋም ግንባታ ሥራ ተጀምሯል ፡፡

### የፕሮጀክት አህጽሮት

| | |
|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | ደብር ቅዱስ ደብረ መዓዛ አቡነ ተ/ሃይማኖት ገዳም የካህናት ማሰልጠኛ ፕሮጀክት |
| አድራሻ | በአርሲ ሀ/ስብከት በአሰላ ከተማ |
| የፕሮጀክቱ ዓላማዎች | • በአርሲ ሀገረ ስብከት ሥር ላሉ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት እንዲሁም ከአጎራባች ሀገረ ስብከት ለሚመጡ ካህናት የስብከተ ወንጌል እና በቴክኒክ ሙያ ክህሎት ሊያገኙባቸው የሚያስችላቸውን ሥልጠና ለመስጠት |
| የፕሮጀክቱ ባለቤት | የአርሲ ሀ/ስብከት |
| የፕሮጀክቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች | በአርሲ ሀገረ ስብከት ሥር እና ላሉ የገጠር አብያተ ክርስቲያናትና ምዕመናን |
| አስፈጻሚ አካላት | በማኅበረ ቅዱሳን የአሰላ ማዕከል እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ |
| ተባባሪ አካላት | ደብረ ቅዱስ ደብረ መዓዛ አቡነ ተ/ሃይማኖት ገዳም |
| የፕሮጀክቱ በጀት | በበጎ አድራጊዎች የሚሸፈን አንደኛ ዙር ________100,000<br>በገዳሙ የሚሸፈን ________29,710<br>በማኅበረ ቅዱሳን አባላት ሙያዊ ድጋፍ____26,354.00 |
| ክትትልና ግምገማ | በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን |



## 10. <u>የብላቴ አውደ ፀሐይ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን የወፍጮ ፕሮጀክት</u>

የብላቴ ዐውደ ፀሐይ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን በሲዳማ ሀ/ስብከት በደቡብሕዝቦች መስተዳደር በወላይታ ዳውሮ ዞን በዱግና ፉንጎ ወረዳ ልዩ ስሙ ብላቴ ጨረቾ በተባለው ቦታ ከአዲስ አበባ 437 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ የቤተክርስቲያኒቱ ይዞታ በትምባሆ እርሻ ልማት ድርጅት እና በብላቴ ጦር ኃይል ማሰልጠኛ ካምኘ መካከል ይገኛል፡፡ በቦታው ላይ የሚገኙት ምእመናን ከፍተኛ በሆነ የመናፍቃን እንቅስቃሴ እና ተፅዕኖ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ በቦታው ላይ የቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚሰጡ ካህናት እንዲሁም ስብከተ ወንጌል የሚያስተምሩ መምህራን ባለመኖራቸው፡ ምእመኑ የቤተክርስቲያናቸውን ትምህርት ካለማወቃቸው የተነሳ እንዲሁም በተለያዩ ተጽዕኖ በመናፍቃን ትምህርት እየተወሰዱ ይገኛሉ ፡፡

ለዚህም ዋናው ምክንያት ቤተክርስቲያኑ የሚተዳደርበት ለካህናትና ለመምህራን የሚከፍለው በጀት ባለመኖሩ ነው ፡፡ ቤተክርስቲያኑ አሁን ያለውን ገቢ የሚያገኘው ከሰበካ ጉባኤ ዓመታዊ ገቢና ክብረ በዓል ለማክበር ከሚመጡ ምእመናን ምፅዋት ሲሆን ይህም ገቢ ከምእመናኑ ቁጥር ማነሣ የተነሳ የቤተክርስቲያኑን ፍላጎት የሚያሟላ አይደለም፡፡ ይህም ክስተት አብዛኞዎቹ በሀ/ስብከቱ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ችግር ነው፡፡ ይህን ችግር በተወሰነ ደረጃ ለመፍታት ይቻል ዘንድ በዚህም ቤተክርስቲያኑና በአካባቢው ላሉ አብያተክርስቲያናት የስብከተ ወንጌልና የአብነት ት/ቤት ማዕከል በማድረግ በመናፍቃን ተፅእኖ ከእናት ቤተክርስቲያናቸው እየኮበለሉ የሚሄዱ ምእመናንን ለመታደግ እንዲቻል በስብከተ ወንጌልና በአገልገሎት ሊሠማሩ የሚችሉ ካህናትና ዲያቆናት በቋሚነት በቦታው ማፍራት ያስፈልጋል፡፡

በዚህም ምክንያት ማኅበረ ቅዱሳን ለቤተክርስቲያኑ ለአንድ የአብነት መምህር ወርሃዊ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ የአካባቢው ልጆች ግብረ ዲቁና እንዲማሩ በማደረግ ላይ ይገኛል ፡፡ ይህንን ጅምር አጠናክሮ ለመቀጠል ይህንን ጊዚያዊ ድጎማ ዘላቂ በሆነ ገቢ ለመተካት ገቢ ሊያስገኝ የሚችል ፕሮጀክት መቅረፅ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የወፍጮ ፕሮጀክት ተቀርጿል ፡፡ ፕሮጀክቱ ተፈፃሚ ሲሆን ቤተክርስቲያኗ መሠረታዊ ወጪዎችን መሸፈን የሚያስችል አቅም እንዲኖራት ያደርጋል፡፡

በአካባቢው ምንም ዓይነት በንግድ ዘርፍ የተሠማራ የኤሌክትሪክ ወፍጮ የለም ፡፡ በአቅራቢያው ከሁለት የማይበልጡ የናፍጣ ወፍጮዎች ያሉ ቢሆንም እነዚህም እህል ብቻ የሚፈጩ ናቸው፡፡ በተለይ በብላቴ ጦር ኃይል ማሰልጠኛ እና በትምባሆ እርሻ ልማት ውስጥ ያሉ ሠራተኞች ካለው የወፍጮ ችግር አንጻር በድርጅቱ በሚመደብ መኪና በሳምንት ወይም በወር ወደ አዋሣ ሄደው ያስፈጫሉ፡፡ ስለዚህ ቤተክርስቲያኒቱ በአካባቢው የእህል ፣የሽሮ እና የበርበሬ ወፍጮ መትከል የገቢ ምንጭ ከማግኘት በተጨማሪ ለአካባቢው ሕብረተሰብ ትልቅ ችግር ይቀርፋል፡፡

### የፕሮጀክት አህጽሮት

| | |
|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | የብላቴ ዐውደ ፀሐይ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ወፍጮ |
| አድራሻ | በወላይታ ዳውሮ ዞን በዱግና ፉንጎ ወረዳ ልዩ ስሙ ብላቴ ጨረቾ |
| የፕሮጀክቱ ዓላማዎች | • ለቤተ ክርስቲያኑ እና ለአካባቢው አብያተ ክርስቲያናት አገልጋይ ካህናት ማፍራት<br>• የቤተ ክርስቲያኑን ካህናትና የአብነት መምህራን ደሞዝ ክፍያ አንድ ዓመት በኃላ በከፊል ለመሸፈን |
| የፕሮጀክቱ ባለቤት | የብላቴ ዐውደ ፀሐይ ቅዱስ ሚካኤል ቤተክርስቲያን |
| የፕሮጀክቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች | የቤተክርስቲያኑ ካህናት፣ መምህራን የቅዳሴ እና ንባብ ተማሪዎች እንዲሁም የአካባቢው ምዕመናን |
| አስፈጻሚ አካላት | በማኅበረ ቅዱሳን የአዋሳ ማዕከል እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ |
| ተባባሪ አካላት | የሲዳማ ሀ/ስብከት |
| የፕሮጀክቱ በጀት | በበጎ አድራጊዎች የሚሸፈን አንደኛ ዙር ________68,550.00<br>በማኅበረ ቅዱሳን አባላት ሙያዊ ድጋፍ____14,683.00 |
| ክትትልና ግምገማ | በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን |

   

## 11. የኪያኬላ አቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም የአብነት ት/ቤት ዘመናዊ የከብት ርባታ ፕሮጀክት

የኪያኬላ አቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም የሚገኘው በከፋ ሀ/ስብከት ከቦንጋ ከተማ በእግር ከ15 ደቂቃ በኃላ በኪያኬላ ቀበሌ ውስጥ ነው፡፡ በሚያዚያ 1987 ዓ.ም ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ መቃኞ ቤት አሠርተው በጥር 1988 ዓ.ም ታቦተህጉ ወደ መቅደሱ ገብቷል ፡፡ በ1994 ዓ.ም የአካባቢው ሕዝበ ክርስቲያን በመተባበር ያስጀመረው አዲስ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን በመገባደድ ላይ ሲሆን ይህ ፕሮጀክትም የሚተገበረው በዚህ ቦታ ላይ ይሆናል፡፡

ይህ ገዳም ከመመሥረቱ አስቀድሞ በአቅራቢያው ቤተክርስቲያን ባለመኖሩ የአካባቢው ምእመን ለክርስትና ፣ለቀብርና ሌሎች መንፈሳዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት ሩቅ መንገድ ይጓዝ ነበር፡፡ በወቅቱ ይህንን የተረዱት ብፁዕነታቸው በዚያ አካባቢ ለሚገኘው ምእመን አንድ ቤተክርስቲያን በአቅራቢያው ለመሥራት ወሰኑ ፡፡ ቀበሌው በሙሉ ፈቃደኝነት ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚውል ቦታ ሰጥቷል ፡፡ ከ1997ዓ.ም ጀምሮ ማኅበረ ቅዱሳን በአካባቢው ያለውን የካህናትና የዲያቆናት እጥረት በመመልከት አንድ የአብነት መምህር በቦታው ላይ መድቦ የአካባቢውን ልጆች የአብነት ትምህርት እንዲማሩ እያደረገ ይገኛል ፡፡

የከፋ ዞን 90% የሚጠጋው ሕዝብ የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ የነበረ ቢሆንም በአሁን ወቅት ግን ባለው ከፍተኛ የኘሮቴስታንት እንቅስቃሴ በተወሰነ ደረጃ ሃይማኖቱን እንዲለውጥ እየተገደደ ይገኛል ፡፡ ስለዚህ ኅብረተሰቡን በሃይማኖቱ እንዲፀና ለማድረግ በተለይም የገጠሩን ኅብረተሰብ በአካባቢው ቋንቋ ሊያስተምሩ የሚችሉ ሰባኪያን ወንጌል ፣ ቀድሰው የሚያቆርቡ ቀሳውስትን እና ዲያቆናትን በፍጥነት ማፍራት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በኪያ ኬላ የሚገኘውን የአብነት ት/ቤት በገቢ ለመደገፍና ቋሚ የገቢ ምንጭ በመፍጠር ለማጠናከር በካህናት/ቀሳውስትና ዲያቆናት እጦት ምክንያት እየተዘጉ የሚገኙ አብያተክርስቲያናትን ለማስከፈት በሰባኪያነ ወንጌል እጥረት የተነሣ ወደ ሌላ ሃይማኖት እየሄደ ያለውን ምእመን ለመጠበቅ አሁን በኪያኬላ ቤ/ክ እያስተማሩ የሚገኙትን የቅዳሴ ንባብ እና ዜማ መምህር ሙሉ አቅም ለማጠናከር ገቢ ሊያስገኝ የሚችል ዘመናዊ የከብት ርባታ ፕሮጀክት ተቀርጿል ፡፡

ገዳሙ ለወተት ላሞች የግጦሽ ቦታ፣ ለበረት ፣ለማለቢያ ቤት የሚሆን በቂ ቦታ አለው፡፡ ስለሆነም ይኸው ኘሮጀክት ተግባራዊ ቢሆን ለኪያኬላና ለቦንጋ ከተማ ቅርብ በመሆኑ እና በአካባቢው ብዙ ተቋማትም በመኖራቸው ለምሳሌ የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋም፣የቴክኒክና ሞያ ማሰልጠኛ ተቋም፣ የጤና ኤክስቴንሽን ማሰልጠኛ፣ሆቴሎች የመንግሥት መ/ቤቶች ከፍተኛ ገበያ ይኖረዋል፡፡ በአጠቃላይ በአካባቢው ያለው የወተት አቅርቦት ውስን በመሆኑ ጠንካራ ገበያ ይኖራል በሚል እሳቤ የተጠና ኘሮጀክት ነው፡፡

### የፕሮጀክት አህጽሮት

| | |
|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | የኪያኬላ አቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም የአብነት ት/ቤት ዘመናዊ ከብት ርባታ |
| አድራሻ | ቦንጋ ከተማ በኪያኬላ ቀበሌ |
| የፕሮጀክቱ ዓላማዎች | • ለገዳሙ ቋሚ የገቢ ምንጭ እንዲኖር ማድረግ<br>• በገዳሙ እየተሰጠ ያለውን የቅዳሴና የንባብ ት/ቤት ማስፋፋት<br>• በመጀመሪያው ዓመት የ10 ተማሪዎችን ሙሉ ወጪአቻውን እንዲሁም የመምህሩን ደመወዝ መሸፈን እና ከሁለተኛ ዓመት ጀምሮ የተማሪውን ቁጥር መጨመር፣ |
| የፕሮጀክቱ ባለቤት | የኪያኬላ አቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም |
| የፕሮጀክቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች | የቤተክርስቲያኑ ካህናት፣ መምህራን፣ የቅዳሴ እና ንባብ ተማሪዎችና የአካባቢው ምእመናን |
| አስፈጻሚ አካላት | በማኅበረ ቅዱሳን የቦንጋ ማዕከል እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ |
| ተባባሪ አካላት | የ ቦንጋ ሀ/ስብከት |
| የፕሮጀክቱ በጀት | በበጎ አድራጊዎች የሚሸፈን አንደኛ ዙር ________182,550.00<br>በማኅበረ ቅዱሳን አባላት ሙያዊ ድጋፍ____18,255.00 |
| ክትትልና ግምገማ | በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን |






## 12. የአበልቲ ምዕራፈ ቅዱሳን ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ገዳም የአብነት ተማሪዎች መኖሪያ ቤት ሁለተኛ ዙር ግንባታ ፕሮጀክት

የአበልቲ ምዕራፈ ቅዱሳን ቅድስት ኪዳነ ምህረት እና አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ገዳም በጅማ ሀ/ስብከት ከአዲስ አበባ በስተ ደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ 200 ኪ.ሜ. ርቀት እንዲሁም ከጅማ ከተማ 146 ኪ.ሜ. በግቤ በረሃ ላይ ይገኛል፡፡ ቤተክርስቲያኑ ከንግስት ዘውዲቱ ጀምሮ የቀደመ ታሪክ ቢኖረውም ጠፍ ሆኖ ቆይቶ በጅማ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ በብጹዕ አቡነ እስጢፋኖስ አማካኝነት እንደገና ተሠርቷል፡፡

በጅማ ሀ/ስብከት በስሩ 12 ወረዳ ቤተክህነት ሲኖሩ በእነዚህም ወረዳዎች ጅማ ከተማን ጨምሮ 284 አብያተ ክርስቲያናት አድባራት እና ገዳማት ይገኛሉ፡፡ ከጅማ ሀ/ስብከት  በተገኘው መረጃ መሠረት ከ284 አብያት ክርስቲያናት ውስጥ 139  በቂ አገልግሎት የማይሰጥባቸው በክብረ በዓል ጊዜ የሚከፈቱ ወይም አንድ ካህን ብቻ ያላቸው ናቸው፡፡ በዚህም የተነሣ ምዕመናኑ ለመናፍቃን እምነት እንዲጋለጡ ሆኗል፡፡ ያሉትም ክርስቲያኖች የቤተክርስቲያን አገልግሎት ለማግኘት ከባድ ፈተና  ሆኖባቸዋል፡፡

ይህንን ችግር በተወሰነ ደረጃ ለመቅረፍ በሀ/ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በብፁዕ በአቡነ እስጢፋኖስ አማካኝነት በአበልቲ ኪዳነምሕረት ገዳም ለሀ/ስብከቱ በኦሮምኛ ቋንቋ አገልጋይ ካህናት የሚያፈራ ማዕከል ተቋቁሟል፡፡ በአሁን ሰዓት  በገዳሙ አርባ አምስት የሚሆኑ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ፣ ይህንን ጅምር ማጠናከር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በማኅበረ ቅዱሳን ለአንድ መቶ የተማሪዎች መኖሪያ ቤት፣ መማሪያ ክፍሎች እና ቤተመጻሕፍት ግንባታ ፕሮጀክት ተቀርጿል፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ 30 ተማሪዎች ሊይዝ የሚችሉ ክፍሎች እና ቤተመጻሕፍ ተገንብቶ ለሀ/ስብከቱ ርክክብ የተደረገ ሲሆን ቀጣዩን ሁለተኛ ዙር ግንባታ ለማስጀምር ድጋፍ አድራጊዎችን በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡

### የፕሮጀክት አህጽሮት

| | |
|---|---|
| የፕሮጀክቱ ስም | የአበልቲ ምዕራፈ ቅዱሳን ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ገዳም የአብነት ተማሪዎች መኖሪያ ቤት ሁለተኛ ዙር ግንባታ |
| አድራሻ | በጅማ ዞን አበልቲ ከተማ |
| የፕሮጀክቱ ዓላማዎች | ገዳሙ በሚገኝበት ሀገረ ስብከት ሥር ላሉ አብያተ ክርስቲያናት አገልጋይ ካህናትና ሰባኪ ወንጌል ማፍራት፡፡<br>በሀገረ ስብከቱ ሥር ከሚገኙ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት 30 ተጨማሪ ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር፡ |
| የፕሮጀክቱ ባለቤት | የጅማ ሀ/ስብከት |
| የፕሮጀክቱ ቀጥተኛ ተጠቃሚዎች | በጅማ ሀ/ስብከት ከሚገኙ አብያተክርስቲያናት የተውጣጡ የንባብ፣ የዜማ እና የቅዳሴ ተማሪዎች |
| አስፈጻሚ አካላት | በማኅበረ ቅዱሳን የጅማ ማዕከል እና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ |
| ተባባሪ አካላት | የአበልቲ ምዕራፈ ቅዱሳን ቅድስት ኪዳነ ምህረት ገዳም |
| የፕሮጀክቱ በጀት | በበጎ አድራጊዎች የሚሸፈን አንደኛ ዙር ________255,550.00<br>በማኅበረ ቅዱሳን አባላት ሙያዊ ድጋፍ____25,583.00 |
| ክትትልና ግምገማ | በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን |

